9ኛ ዓመት ቁጥር 15
9th Year No. 15

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th April, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.80
Unit price 3.80

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 102/1996 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

Content

Proclamation NO. 102/2004
The Amhara National Regional State Financial Administration Amendment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 102/1996 ዓ.ም.
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የበጀት ማሻሻያ ፕሮግራሙን ተፈፃሚነት ለማሳለጥና የሲቪል ሰርቪሱን የአገልግሎት አሠጣጥ ሥርዓት ይበልጥ ለማሻሻል ይቻል ዘንድ በሥራ ላይ ያለውን የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 ዓ.ም /እንደተሻሻለ/ እንደገና ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት በክልሉ ሕገመንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 መሠረት የሚከተለውን አውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንደገና ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 102/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Proclamation NO.102/2004
A Proclamation Issued to Amend the Financial Administration of the Amhara National Regional State

WHEREAS, it is necessary to re-amend the Amhara National Regional State Finance Administration Proclamation (as amended) No. 18/1997 which is in effect with a view to facilitating the implementation of the budget reform program and to better improving the service delivery system of the civil service;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional State, in accordance with Article 49 Sub-Article 3(1) of the Constitution of the Region, hereby proclaims the following.

1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Financial Administration Proclamation Re-amendment Proclamation No.102/2004."

2. ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 18/1989 ዓ.ም. /እንደተሻሻለ/ በሚከተለው አኳኋን እንደገና ተሻሽሏል።

ሀ. የአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 1 ተተክቷል።

1. በመንግስት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር መደበኛ በጀትን በሚመለከት ከአንድ የሥራ ክፍል ወደ ሌላ የሥራ ክፍል እንዲሁም በሥራ ክፍል ውስጥ የሚደረግ ዝውውር እስከሆነ ድረስ የቢሮ ኃላፊው በጀትን ለማዛወር ያለውን ሥልጣን በውክልና አግባብ ላለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ ሊሠጥ ይችላል።

ለ. የአዋጁ አንቀጽ 19 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 19 ተተክቷል።

19. ቢሮው በሚከተሉት ምክንያቶች የአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት መደበኛ ወይም ካፒታል በጀት ወደ ሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት መደበኛ ወይም ካፒታል በጀት እንዲዛወር ሊፈቅድ ይችላል፡-

1. በመንግሥት መሥሪያ ቤት የፀደቀ የመዋቅር ለውጥ ወይም የሥራ ኃላፊነት ማሻሻያ በመደረጉ ምክንያት የበጀት ዝውውር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

2. በአንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ውስጥ ያጋጠመን የመደበኛ ወይም የካፒታል በጀት እጥረት ለማቃለል ከሌላ የመንግስት መሥሪያ ቤት የተፈቀደ የመደበኛ ወይም የካፒታል በጀት በማዘዋወር መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝና ይኸውም ዝውውር ያስፈለገው ቀደም ሲል ለተፈቀደ ወይም ላልተፈቀደ መደበኛና ካፒታል በጀት ሲሆን።

2. Amendment

The Amhara National Regional State Financial Administration Proclamation (as amended) No. 18/1997 is hereby re-amended as follows:

A. Provision of Sub-Article 1 of Article 18 of the Proclamation is hereby deleted and replaced with the following new sub-Article.

1. As budget transfer made in a government office with regard to recurrent budget is transfer of same from one department to another department as well as within a department, the Head of the Bureau may entrust the power of budget transfer vested in him to the chief of a relevant government office through delegation.

B. Article 19 of the Proclamation is hereby deleted and replaced with the following new Article 19.

19. The Bureau may permit to transfer recurrent or capital budget of a government office to another government office's recurrent or capital budget due to the following reasons:

1. Whenever it is found necessary to make budget transfer because of approved structural change or improvement made in job responsibility in a government office:

2. Whenever it is found necessary to transfer and use recurrent or capital budget allowed from another government office so as to overcome recurrent or capital budget deficit happened in a government office and the transfer of same is necessary for recurrent or capital budget which is priorly appropriated or non-appropriated.

3. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህርዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

3. Effective Date

This Proclamation shall come into force commencing the date of its publication in the *Zikre Hig Gazzeta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 20th day of April, 2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region